ፕሬስ የሕዝብ ዘብ ነው

# ጦቢያ

ጦቢያ፣ 6ኛ ዓመት ቁ. 6 ጥር 1991

## ኢትዮጵያና ኤርትራ ከእንግዲህ ወዴት? እንዴት?

መድረክ (ለመነጋገሪያ)

- «አሥመራ እንገናኝ»

ስንሻው ተገኝ


- ነባር እሴትና አዲስ አሳብ

ጸጋዬ ገ/መድኅን አርአያ

- የኤርትራ የዜግነት ቀውስና ምንጩ

ከባህታ



«ሕገ - መንግሥቱ በተጨባጭ የመድብለ ፓርቲን ሥርዓት አይፈቅድም»

ዶ/ር ነገደ ጎበዜ

- የልጅ ኢያሱ እስርና አሟሟት

(ከዓይን ምስክሮች)

# ቃለ - መጠይቅ ...

ከገጽ 18 የዞረ

እየተዘጋጀበት እንደሆነ እያወቅን እኛም ዝም ብለን አንቀመጥም:: ከፓርላማው ወንበሮች ከ98 ከመቶ በላይ እየተቆጣጠረም ቢሆን ነጻ ምርጫ አካሂጃለሁ እያለ ሲከራከር ቢቆይም ፈረንጆች «ተው እያስመ ሰልክ ነው» ብለው መጨቅጨቅ ላይ እንደሆኑም እናውቃለን:: የተገኘው ዘዴ ለታማኝና ራሱ በቅድሚያ ይስማሙኛል ብሎ ለመረጣቸው ተቃዋሚዎች ከፓርላማው ወንበር አስርም፣ ሃያም ከመቶ በቅድሚያ ተቋርጦ ማስገባትም እንደሆነ ከብዙ ምንጮች ዜናዎች ደርሰውናል:: ከመጪው ምርጫ አንጻር አንዱ ተግባራችን ይህንን ሴራ ነቅቶ መታገልና ርቃኑን እስኪቀር ማጋለጥ መሆን ይኖርበታል:: የዚህ ትግላችን ስኬታማነት የሚለካው እስከዚህም ድረስ የዛሬ ዓመት ተኩል ያልተጭበረበረ ምርጫ በመካሄዱ አይደለም:: ቁም ነገሩ ሴራውና ተባባሪዎቹ ከወዲሁ መጋለጣቸውና በተቃዋሚዎች ሰፊር ክፍፍልን በሕዝባችን መንፈስ ውዥንብርን ለመንዛት የሚያደርጉት ርኩስ ጥረት ከወዲሁ ከሽፎ ለቀጣዩ ትግል አመቺ ሁኔታ መፈጠሩ ላይ ነው::

በመሆኑም መጭውን ምርጫ በተመለከተ ይህንን ሤራ ከማጋለጡ ትግል ጋር ተያይዞ ስለሚጠብቀን ትግል የኢተፖድህ ዓላማ ግልጽ ሆኖ መቀመጥ አለበት::

አንደኛ የፓሪስ ሰነዳችን ላይ ነጻ ምርጫ ስንል ዛሬ ድፍን ዓለም ስለተቀበላቸው መስፈርቶች በመነሳት ምን ማለታችን እንደሆነ በግልጽ አስቀምጠናል:: አንዳንድ ፈረንጆች «ይህ ለእኛ ለሰለጠንነው እንጂ ለእናንተ አይሠራም ለዚያውም እኛ እዚህ የደረስነው መቶም ሁለት መቶም ዓመት ኳትነን ነው» እንደሚሉ እኔም እራሴ አጋጥሞኛል:: ግን ለዲፕሎማሲው ትግል ተገቢ ቦታውን ብንሰጠውም የእኛ መንቀሳቀሻ (Constituency) የኢትዮጵያ ሕዝብ እንጂ እነሱ ስላልሆኑ በዚህ ክርክራቸውና ምክራቸው ልባችን መከፈል የለበትም:: በመሆኑም ሕዝባችን በነዚህ መስፈርቶች ዙሪያ ተሰባስቦና ተደራጅቶ እንዲታገል ጥረት ማድረግ ይኖርብናል:: የ1992 ዓም ቀጠሮ የሚጠይቀው ካሁኑ ለነዚህ መስፈርቶች መሟላት እጥፍ ድርብ ትግል ማካሄድ እንጂ ከወዲሁ «አንሳተፍም» ብሎ አስቸጋሪና ውስብስብ ከሆነው የትግል መስክ ራስን ማግለል ወይም ደግሞ «እንሳተፋለን» ብሎ ከወዲሁ እጅ መስጠት አይደለም::

ሁለተኛ ደግሞ በፓሪሱ ሰነድ ላይ የተቀመጡት ዓለም አቀፋዊ መስፈርቶች መቶ በመቶ የመሟላታቸው ወይም ያለመሟላታቸው ጉዳይ አለ:: ለእኛ ዋናው ጥያቄ ሕዝባችንና ታጋይ ዲሞክራሲያዊ ኃይሎች እነዚህን መስፈርቶች አንግበው ወያኔን መታገላቸውና ወደ ፊት መራ መዳቸው ላይ ነው:: በትግሉ ሂደት ውስጥ ሕዝቦችንን ከጐናችን አሰልፈን በምናደርገው ጉዞ ትግላችን ምን ያህል ወደፊት እንደተራመደ፣ ይህ ትግላችን ምን ያህል ፍሬ እንደሰጠ በየወቅቱ መገምገም ይኖርብናል:: በትግላችን ባገኘነው ፍሬ ተመርኩዘን ምርጫ ውስጥ መሳተፋችን ለዲሞክራሲ የሚደረገውን ትግል ያግዛል ብለን ከገመትን እንሳተፋለን:: ሁኔታዎች በበቂ አልተሟሉም:: እዚህ ምርጫ ውስጥ መሳተፍ የሃገራችንን ዲሞክራቶች ይከፋፍላል:: ሕዝባችንንም ግራ ያጋባል፣ የወያኔን ፀረ ዲሞክራቲክ አገዛዝ እድሜ ያራዝማል ብለን ከገመትን ግን ምርጫው ውስጥ አንገባም:: ባለፈው መስከረም መጨረሻ ላይ የኢተፖድህ አመራር የውስጥም የውጭም ተወካዮች አምስተርዳም ከተማ ባደረግነው የሥራ ስብሰባ ላይ ሁኔታዎችን ገምግሞ የመሳተፍ ወይም ያለመሳተፉ ጥያቄ የሚወሰነው በጋራ እንዲሆን መስማማታችን መጭውን ትግል ከውዥንብር የሚጠብቅ፣ ኃላፊነት የተመላበት ውሳኔ ነው እላለሁ::

ለመጭው ምርጫስ ምን ያህል ተዘጋጅታችኋል? ለተባለው በበኩሌ ዋናው ጥያቄ ይህ ሆኖ አይታየኝም:: ዛሬ በሃገራችን ካሉ የፖለቲካ ኃይሎች ሁሉ ለነጻ ምርጫ ያልተዘጋጀ አንድ ኃይል ቢኖር ወያኔ ነው:: የሃገራችን ችግሮች ዋና ገጽታ ይህ ቡድን ለነጻ ምርጫ አለመዘጋጀት ነው:: ዛሬ በሃገራችን የሚደረገው ትግል ለዲሞክራሲ ያመቸ የኃይል ሚዛን በመፍጠር ይህ ቡድን ለነጻ ምርጫ እንቅፋትነቱ እንዲያከትም የሚደረግ ትግል ነው:: እርግጥ የተቃዋሚዎች የመዘጋጀትና አለመዘጋጀት ጉዳይ እንደ ቀላል ነገር አይታይም:: ነገር ግን አፈናና ግድያ ቆመው፣ የመደራጀት ሙሉ መብት ተረጋግጦ፣ በሃገሪቱ በሙሉ በይፋ መንቀሳቀስ፣ ጽ/ቤቶችን መክፈትና ቅስቀሳ ማድረግ የሚችሉበት ሁኔታ ከተፈጠረ በአጭር ጊዜ ውስጥ ተቃዋሚዎች ቢያለበት ሊክተሉ ይችላሉ የሚል እምነት አለኝ::

የዛሬው ትኩረታችን ይህ ለዘመናት በተፈራረቁበት አገዛዞች ግፍ ጀርባው የተላጠ የኢትዮጵያ ሕዝብ ዛሬ በደርዘን የሚቆጠሩ የአፍሪካ አገሮችን ጨምሮ ድፍን ዓለምን በማላበስ ላይ ካለው የዲሞክራሲ ጸጋ ተነጥሎ የሚዋረድበት ምንም የተለየ እርግማን እንደሌለበት ተገንዝቦ ለትግል እንዲነሳ ማድረጉ ላይ ነው:: ለነጻ ምርጫ የተመቻቸ ዲሞክራሲያዊ የኃይል ሚዛን ለመፍጠር የሚደረገው ትግል ሕዝባችን በታሪኩ ለመጀመሪያ ጊዜ ሕልሙ፣ ፍላጐቱና ድምፁ የሚደመጥበትና ከቁጥር የሚገባበትን ሁኔታ በራሱ ታግሎ እንዲያመቻች ለማገዝ ነው:: ዛሬ ከምንገኝበት የትግል ምዕራፍ ከወዲሁ ይህንን ወይም ያንን የፖለቲካ ቡድን ለሥልጣን የማብቃቱ ጉዳይ ቅድሚያ ከተሰጠው የኢተፖድህን የትግል ዓላማ ያጠበውና ለትግሉ ሊሰበስብ የሚችለውንና የሚገባውን ኃይል ይቀንስበታል::

ኢተፖድህ ነጻ ምርጫ ብቻ አይደለም:: ለዲሞክራሲ ሂደትና ለነጻ ምርጫ የቆመና ለዚህ የሚታገል ስብስብ ነው:: የሕብረት ትግሉ ዋና ዓላማ በምርጫ ከመሸናነፍ ዘልቆ የሚሄድ የዲሞክራሲን መሰፈን የሚጠይቅ ዓላማ ነው:: ዲሞክራሲያዊ ሕብረተሰብ ለመፍጠር የሚደረገው ትግል የፖለቲካ ስብስቦች እንዲደራጁ፣ እንዲያብቡና በምርጫ እንዲሳተፉ የሚደረግ ትግል ብቻ አይደለም:: የሙያና ሌሎች የሲቪክ ስብስቦች፣ የኢኮኖሚ ጥቅምንም ሆነ የባህልና የህልውና መብቶችን ለማስከበር የሚሹ ኃይሎች በየመስኩና በየፈርጁ እንደልብ ለመደራጀት የሚችሉበት አካባቢ የመፍጠሩም ጉዳይ ከትግላችን አጀንዳ ውስጥ የሚገባ ጉዳይ ነው:: የሲቪል ማህበረሰብ መደራጀትና ማበብ ለዲሞክራሲ መኖር የማያሳስት ምልክት ብቻ አይደለም:: ለዲሞክራሲ ስር መስደድም እንደዋስትና የሚታይ ጉዳይ ነው:: በመሆኑም ኢተፖድህ የትግል አድማሱን ከምርጫ ጥያቄ ሰፋ አድርጐ ከሌሎችም የሙያና የተለያዩ ማህበራት ጋር ትግግዝ የሚፈጥርበትን ሁኔታ ማጥናት ይኖርበታል::

ዞሮ ዞሮ በዚህ መልክ የምንታገልለት የዴሞክራሲ ሁኔታ ከተፈጠረና በዚህ ሁኔታ ነጻ ምርጫ መካሄድ ከቻለ ይህንን ምርጫ ማንም ያሸንፍ ማን የኢተፖድህ ተልዕኮ ተሳካ፣ ትግሉም አሸነፈ ማለት ይቻላል:: በዚህ ምርጫ ወያኔ ቢያሸንፍ እንኳን ደረት የሚያስመታ ነገር አይኖርም:: የነጻ ምርጫ መካሄድ ራሱ የመላ የሃገራችን ሕዝቦች ድል ነው ብለን እንቆጥረዋለንና::

**ጦቢያ:-** ወደ አገር ቤት ገብታችሁ ለመታገል የምትችሉት ወያኔ/ኢህአዴግ ያወጣቸውን ሕጐች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎች፣ ፖሊሲዎችና ሕገ መንግሥቱን ለመቀበል ስትስማሙ መሆኑ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ገልጸዋል:: ይህን ጉዳይ እንዴት ያዩታል?

**ዶ/ር ነገደ:-** ወያኔ ያወጣቸውን ሕጐች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎች፣ ፖሊሲዎችና ሕገ መንግሥቱን ሁሉ ከተቀበልን እኛስ ምኑን ተቃዋሚ ሆንነው? ተለጣፊዎችና ታማኝ ተቃዋሚዎችስ ምን ይቀራቸዋል? የዲሞክራሲ ሂደትና የነጻ ምርጫ ትልም የሚለው ሰነዳችን ለዚህ በቂ መልስ የሚሰጥ ይመስለኛል:: ነጻ ምርጫ ከተባለ ፕሬስ ያስፈልጋል ብለናል:: ይህን ስንል የፕሬሱ ሕግ ተቀባይነት የለውም ይቀየር ማለታችን ነው:: ነጻ ምርጫ ከተባለ በዓለም አቀፍ መስፈርቶች መሠረት የዚህ አንዱና ዋናው መልኩ የዜጐች ሁሉ የመምረጥም የመመረጥም መብት ማለት ነው ብለናል:: ይህም ማለት ዘረኛ የሆነውን፣ ለአንዱ ዜጋ የመምረጥም የመመረጥም መብት ሰጥቶ ለላውን ዜጋ ደግሞ የመምረጥ እንጂ የመመረጥ መብት ተነፍገዋል የሚለውንና በሃገራችን አንደኛና ሁለተኛ ማዕረግ ዜጐች የተከለውን ዘግናኝ የምርጫ ሕግ እንቃወማለን ማለት ነው:: ወያኔ ሆን ብሎ የመረጠው የምርጫ ሥርዓት ከያለበት አናሳ ጉሰኞችን ፓርላማ ውስጥ የሚያጠራቅም፣ ዘረኝነትን የሚያጠናክርና የሃገራችንን አንድነት የሚበረብር የምርጫ ሥርዓት ነው:: ከመጀመሪያው የፓሪስ ጉባኤ ጀምረን ይህንን የምርጫ ሥርዓት ተቃውመናል:: በሱ ፈንታ ከካምቦዲያ እስከ ደቡብ አፍሪካ ድረስ በሽግግር ላይ ላሉ ህብረተሰቦች ፍቱንነቱን ባስመሰከረው፣ የሃገርን አንድነት ከምርጫ ምርጫ እያጠናከረ በሚሄደው የተመጣጣኝ ውክልና ሥርዓት እንዲተካ እንታገላለን::







እነዚህን ለምሳሌ ያህል አነሳኋቸው እንጂ ሌሎችም ብዙ ነጥቦች አሉ:: በዚሁ መጽሔታችሁ ላይ ቀደም ሲል ረዳት ፕሮፌሰር መረራ ጉዲና፣ በኋላም በኢትዮጵያ የኢተፖድህ ጽ/ቤት ሰብሳቢ አቶ ክፍሌ ጥግነህ አባተ እንዲሁም በቀስተ ደመና ሬዲዮ ዶ/ር በየነ ጴጥሮስ ያስቀመጧቸው ነጻና ገለልተኛ የሆነ የምርጫ ቦርድ መቋቋምን፣ የድርጅቶች እንደልብ የመንቀሳቀስ መብት መከበርን፣ የፖለቲካና የህሊና እስረኞች መፈታትን የመሳሰሉ ቁም ነገሮችም እንዳሉም መረሳት የለበትም::

እነዚህን ሁሉ ነጥቦች እንዲሟሉ በግልጽ እየጠየቅንና እየታገልን በተቀኛነት የምንጠረጠርበት ምንም ምክንያት የለም:: የእኛ ችግርና ጠብ ተቀጥላ ሆናችሁ ከሚሉን ጋር ሳይሆን የጥያቄዎቹንና የቅድመ ሁኔታዎቹን መብዛት አይተው በአክራሪነት ሊወነጅሉን ከሚከጅላቸው የወያኔ ደጋፊዎች ጋር ነው:: ግን ልብ ብሎ ለሚመለከት ሰው አንድ ነገር ግልጽ መሆን አለበት:: እነዚህን ነጥቦች ሁሉ መደርደራችን የሚያሳየው የእኛን «አክራሪነት» አይደለም:: ይሟሉ፣ ይቀየሩ፣ ይሻሻሉ እያልን የምንደረድራቸው ነጥቦች መብዛታቸው የሚያሳየው አንድ ነገር ቢኖር በወያኔ/ኢህአዴግ ሥር ሃገራችን ምን ያህል ለነጻ ምርጫ ከተመቻቸ ሁኔታ ርቃ እንደምትገኝ ብቻ ነው:: እንደዚህ ያለ ሁኔታ ላይ እየተገኘን «ነገሮች ከምርጫ ምርጫ ቀስ በቀስ እየተሟሉ ይሄዳሉና በመጪው ምርጫ ተሳተፉ» የሚሉን ኃይሎች ካሉ ይህ ምክራቸው ከአንድ ገደል ጫፍ ሌላ ገደል ጫፍ እያረፋችሁ ዝለሉ የሚል ዓይነት አደገኛ ምክር በመሆኑ እኛም አንቀበለውም:: የኢትዮጵያም ሕዝብ አይቀበለውም::

በሕገ መንግሥቱም ጉዳይ ከተቃውሞ ሌላ ምንም አቋም ሊኖር አይችልም:: በአንድ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ክልል ውስጥ አንድ ሕገ መንግሥት በሕዝብ ተቀባይነት አግኝቷል ቢባል እንኳን ሁለት ዓይነት ተቃዋሚ ኃይሎች ሊኖሩ ይችላሉ::

አንደኛው ዓይነት የተቃውሞ ኃይል ያለውን ሕገ መንግሥት ተቀብሎ በዚህ ሠነድ ክልል ውስጥ የራሱን አማራጭ የፖለቲካ ፕሮግራም ለሕዝብ ድምጽ በማቅረብ በሕዝብ ድጋፍ የመንግሥት ሥልጣን ለመያዝና ፕሮግራሙን በተግባር ለማዋል ሲል ያለውን መንግሥት የሚቃወምና የሚታገል የተቃውሞ ኃይል ነው::

ሁለተኛው የተቃውሞ ኃይል ሕገ መንግሥቱን ራሱን ተቃውሞ በተወሰኑ ነጥቦች ላይ እንዲሻሻል ወይም ደግሞ ጨርሶ እንዲለወጥ የሚታገል የተቃውሞ ኃይል ነው::

በእኛ አገርና በኢህአዴግ ሕገ መንግሥት ሥር ሊኖር የሚችለው ተቃውሞ ይኸ ሁለተኛው ዓይነት ተቃውሞ ብቻ ነው:: ምርጫ አሸንፌ፣ የመንግሥት ሥልጣን ይዤ የተሸነፈውን መንግሥት የፖለቲካ ፕሮግራም ቀይሬ የራሴን የተመረጥሁበትን አማራጭ ፕሮግራም በሥራ ላይ አውላለሁ የሚለው የመጀመሪያው ዓይነት ተቃውሞ ምንም ትርጉም የለውም::

ባንዳን ይህንን ሕገ መንግሥት ገና የተጻፈበት ቀለም ሳይደርቅ ከዋናው ባለጉዳይ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ተሽቀዳድመው «ዲሞክራሲያ ሕገ መንግሥት ነው» ብለውታል:: እኔ ይህን ሰነድ ሳይ ከሰላሳ ዓመት በፊት በሕግ ፋኩ ልቲ የመጀመሪያ ዓመት የሕገ መንግሥት ኮርስ ላይ «ስታሊናዊ ሕገ መንግሥት፣ በቲዎሪና በተግባር» በሚል ርእስ ወደተሰጠን ትምህርት ነው የተመለስኩት:: ይህ ሕገ መንግሥት እንዴትና ለምን ከ1936 ዓም የስታሊን ሕገ መንግሥትና ከ1980 ዓም የኮሎኔል መንግሥቱ ሕገ መንግሥት እንደ ሁለት ጠብታ ውሃ እንደሚመሳሰልና ለምንስ ለሃገራችን ሰላምና አንድነት አደገኛ ሰነድ እንደሆነ «የኢህአዴግ ሕገ መንግሥት ሲመረመር» በሚል ርእስ ኢዴሃቅ ተችቶብታል:: እዚህ ላይ አልመለስበትም::

በያዝነው በምርጫ ጥያቄ አንጻር ስናየው ግን አንድ በግልጽ ማለት የሚቻል ነገር አለ:: በፓሪሱ ሰነዳችን በትክክል እንደተቀመጠው ሕገ መንግሥቱ በተጨባጭ የመድብለ ፓርቲን ሥርዓት አይፈቅድም:: ይህ ሕገ መንግሥት ስታሊናዊው የሕገ መንግሥት ቲዎሪ «ፕሮግራማቲክ ፖዘቲቪዝም» በሚለው ጽንሰ ሃሳብ መሠረት «ተራ» ሕገ መንግሥት ሳይሆን የፈረንሣይ የሕገ መንግሥት ምሁራን «ፕሮግራም ሕገ መንግሥት» ብለው የሚፈርጁት ሰነድ ዓይነት ነው:: የአንድን ፓርቲ የፖለቲካና ርዕዮተ ዓለማዊ ራእይ፣ የአንድ ፓርቲ የሶሻልና የኢኮኖሚ ፖሊሲ የሃገሪቱ የበላይ ሕግ ብሎ በሕብረተሰቡ ላይ የሚጭን ሰነድ ነው::

በዚህም የተነሳ ከፍ ብዬ እንዳልኩት በዚህ በአንድ ፓርቲ ሕገ መንግሥት ሥር የመድብለ ፓርቲ ምርጫ ጨርሶ ትርጉም የሚያጣበት ሁኔታ ይፈጠራል:: መጀመሪያ ነገር ይህንን ሕገ መንግሥት መቀበል ማለት የወያኔን የፖለቲካ ፕሮግራም መቀበል ማለት ይሆናል:: ሕገ መንግሥቱን እንቀበላለን ግን የወያኔን ፖሊሲዎች ተቃውመን በምርጫ የእኛን ፖሊሲ ከሥራ ላይ እናውላለን የሚሉ ኃይሎች ካሉ «ምርጫ አሸን ፎስ የት ለመድረስ?» የሚለው ጥያቄ ወዲያውኑ ከፊታቸው እንደሚደቀን ግልጽ ይመስለኛል:: ለምሳሌ ሕገ መንግሥቱ መሬት የመንግሥት ነው ይላል:: በዚህ ለሕብረተሰባችን ወሳኝ በሆነ ጥያቄ ላይ «መሬት የግል ሀብት» ይሁን ብሎ የሚነሳ ተቃዋሚ ኃይል በተዓምር ወያኔን በድምጽ ብልጫ አሸንፎ ሥልጣን ቢይዝ እንኳን የኢህአዴግ ሕገ መንግሥት እስከ ጸና ድረስ የራሱን ትቶ የኢህአዴግን የመሬት ፖሊሲ በተግባር ማዋል ይገደዳል ማለት ነው:: የተመረጠበትን ፕሮግራም በሥራ ላይ ለማዋል ወያኔን ብቻ ሳይሆን የወያኔንም ሕገ መንግሥት «ማሸነፍ» ይገደዳል::

በዚህ ሕገ መንግሥት ሥር የብዙ ፓርቲዎች ለሥልጣን መፎካከር ትርጉም እንደሌለው የተለያዩ ፓርቲዎችና የፖለቲካ ፕሮግራሞች በሥልጣን መፈራረቅ እንደማይቻል ዛሬ እንኳን እኛ የኢህአዴግ መሪዎችና ደጋፊዎችም የተገነዘቡት ይመስላል:: ከዚህ ሁኔታ ለመገላገል የሚሰነዘሩት መከራከሪያ «ተወዳድራችሁ አሸንፉና ሕገ መንግሥቱንም አሻሽሉ፣ ቀይሩ» የሚል የማያዋጣ መከራከሪያ ነው:: ይህ ሕገ መንግሥቱን የማሻሻል ጉዳይ ለምሳሌ በመጀመሪያው ረቂቅ ላይ እንደነበረው በሬፈረንደም የሚቻል ቢሆን ኖሮ በእውነቱ ምንም ችግር አይኖርም ነበር:: ግን እሱ ቀርቶ የማሻሻሉ ሂደት በጣም ከመቆላለፉ የተነሳ አሁን ባለው ሁኔታ ድፍን የኢትዮጵያ ሕዝብ ይህ ሕገ መንግሥት እንዲሻሻል ድምጹ ቢሰጥ እንኳን ከሕዝቡ ሩብ ከመቶ የማይሆነው የሐረር ክልል አሻፈረኝ ካለ ሕገ መንግሥቱ የሚሻሻልበት ሁኔታ የለም:: ይህ ሕገ መንግሥት ፀረ ዲሞክራቲክ ብቻ ሳይሆን አደገኛ ነው ያልነውና በፓሪሱ ሰነዳችን ላይ የሕገ መንግሥት ማሻሻሉ ሂደት ዲሞክራሲያዊ እንዲሆን የጠየቅነው ለዚህ ነው::

ባጭሩ በወያኔ ሕገ መንግሥት አንጻር ሊኖር የሚችለው ተቃውሞ ከላይ ያልኩት ሁለተኛው ዓይነት ሕገ መንግሥቱ እንዲሻሻልና እንዲለወጥ የሚጥር ተቃውሞ ብቻ ነው:: ይህም ደግሞ የአንድ ሕዝብና ይህንን ሕዝብ የሚወክሉ ተቃዋሚ ኃይሎች የማይገሰስ ዲሞክራሲያዊ መብት ነው:: ከጥቂት ዓመታት በፊት «ህገ መንግሥቱን ካልተቀበላችሁ.....» ሲሉ የነበሩት ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ እንኳን ዛሬ ቀልብ ገዝተው በሰላማዊ ዘዴ እስከሆነ ድረስ ሕገ መንግሥቱንም እየተቃወሙ በፖለቲካው ሂደት ውስጥ መሳተፍ እንደሚቻል የተቀበሉ ይመስላል::

ይህ ሁሉ ግልጽ ከሆነ ዘንዳ አንድ ሁለት ነገሮችን ማለት እፈልጋለሁ:: መጀመሪያ ነገር ግን መንግሥቱን አንቀበለውም:: ምርጫ በዚሁ ሕገ መንግሥት ሥር ትርፍ ልፋት ነው ስለተባለ ከላይ ስለምርጫ ቅድመ ሁኔታዎች የተዘረዘሩት ነጥቦች ከተሟሉ «ሕገ መንግሥቱ እስኪሻሻል ወይም እስኪለወጥ ድረስ ምርጫ ሂደት ውስጥ አንሳተፍም» ማለት አይደለም:: አንድ ምርጫ ነጻና ዲሞክራሲያዊ እንዲባል ምን ምን መስፈርቶች መሟላት እንዳለባቸው በሰነዳችን ላይ እንዳስቀመጥን ሁሉ አንድ ሕገ መንግሥትም ዲሞክራሲያዊ እንዲባል ምን ምን መስፈርቶችን ማካተት እንዳለበት በግልጽ አስቀምጠናል:: እነዚህ ነጥቦች በሃገራችን ሕገ መንግሥት ውስጥ የሚካተቱት እኛ ቤት ዘግተን ከወያኔ ጋር በመወያየታችን ሳይሆን የኢትዮጵያን ሕዝብና የሃገራችንን ታጋይ ኃይሎች አንቀሳቅሰን ወያኔና ሕገ መንግሥቱን ስንታገል ነው:: በመሆኑም የምርጫ ሁኔታዎች ተሟልተዋል ብለን ከገመትን ምርጫው ውስጥ ይህንን ሕገ መንግሥት ለማጋለጥና የኛን አማራጭ ለሕዝብ ለማስጨበጥ የማንሳተፍበት ምክንያት አይኖርም::

ሁለተኛው ነጥብ «አለቅጥ ቅድመ ሁኔታዎች አንዛዛችሁ፣ ትንሽ አበዛችሁት፣ ወያኔ ይህንን ሁሉ መቀበል ያስቸግረዋል:: ስለዚህ «የሚመስል ነገር ብቻ ብትጠይቁ ይሻላል» የሚሉ አንዳንድ ወገኖች ሊኖሩ ይችላሉ:: «አበዛችሁት» ሊባል የሚቻለው እነዚህ ነጥቦች ከወያኔ ብንለምን ነበር:: እኛ ግን የተነሳነው ግልጽና ዲሞክራሲያዊ ዓላማችንን ይዘንና ይህንን ለሕዝብ አስጨብጠን ወያኔን መታገል ስለሆነ «ብዙ» የሚባል ነገር ሊኖር አይችልም:: ■